# ሁሉም ዓይነት የዘር ልዩነቶች ለማስወገድ የተደረገ ዓለም አቀፍ ስምምነት

## ይህንን ስምምነት የተቀበሉ ሀገራት፤

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቻርተር በተፈጥሯዊ የሰው ልጅ ክብርና እኩልነት መርሆዎች መመስረቱን፤ እንዲሁም ሁሉም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባል ሀገራት ድርጅቱ የተመሰረተበት ዓላማ፤ ማለትም ምንም ዓይነት የዘር፣ የቀለም፣ የጾታ፣ የቋንቋ ወይም የሃይማኖት ልዩነት ሳይደረግ የማንኛውም ሰው ሰብአዊ መብቶችና መሰረታዊ ነጻነቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ ለማስከበርና ለማጋገጥ ከድርጅቱ ጋር በመተባበር በግልና በጋራ እርምጃ ለመውሰድ የገቡትን ቃል ኪዳን ግምት ውስጥ በማስገባት፤

የሰብአዊ መብቶች ዓለም አቀፍ መግለጫ ሁሉም ሰብአዊ ፍጡር ነጻ መሆኑን፤ እኩል ሰብአዊ ክብርና መብቶች ተጎናፅፎ መወለዱን፤ ማንኛውም ሰው ምንም ዓይነት የዘር፣ የቀለም ወይም የማኅበራዊ ኑሮ ደረጃ ማበላለጥ ሳይደረግበት በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ የሰፈሩ መብቶች መጎናፀፍ እንዳለበት መደንገጉን በመገንዘብ፤

ሁሉም የሰው ልጆች በሕግ ፊት እኩል መሆናቸው፣ አድልዎ እንዳይደርስባቸውና አድልዎ እንዲፈጸምባቸው ግፊት እንዳይደረግባቸው እኩል የሕግ ከለላ መጎናፀፍ እንዳለባቸው በመረዳት፤

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በማንኛውም ቦታ በማንኛውም መልኩ የሚከሰት ቅኝ አገዛዝና ከእሱ ጋር የተሳሰሩ ሁሉም የአድልዎና የማበላለጥ መልኮች ማውገዙን፤ እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 14 ቀን 1960 የወጣውና የተባበሩት መንግሥታት (አጠቃላይ ጉባኤ ውሳኔ 1514 /XV/) በቅኝ ግዛት ስር የሚገኙ ሀገራትና ሕዝቦች ነጻነት የሚያጎናፅፈው መግለጫ፤ እነዚህ ሕዝቦች በአስቸኳይና ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ነፃነታቸውን እንዲቀዳጁ ማረጋገጡን በይፋ ማወጁን ግምት ውስጥ በማስገባት፤

እ.ኤ.አ. ኖቬምበር 20 ቀን 1963 ሁሉም ዓይነት የዘር ልዩነቶች ለማስወገድ የወጣው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አዋጅ (አጠቃላይ ጉባኤ ውሳኔ 1904 /XVII/) የዘር ልዩነት ከሁሉም መልኮቹና መገለጫዎቹ ከመላው ዓለም በአፋጣኝ እንዲወገድና የሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ክብር እንዲጠበቅና ዋስትና እንዲያገኝ በይፋ ማረጋገጡን በመገንዘብ፤

በዘር ልዩነት የተመሰረተ የበላይነት መርህ በሳይንስ ረገድ ስህተት፣ በሞራል በኩል የተወገዘ፣ በማኅበረሰብ ረገድም ኢ-ፍትሐዊና አደገኛ መሆኑ እና በፅንሰ ሃሳብም ሆነ በተግባር ለዘር ልዩነት መነሻ የሚሆን ሕጋዊ መሰረት የሌለ መሆኑን በማመን፤

በዘር፣ በቀለም ወይም በትውልድ ሃረግ በመመስረት በሰዎች መካከል የሚፈጠር አድልዎ በሀገራት መካከል በወዳጅነት የተመሰረተ ሰላማዊ ግንኙነት እንዳይኖር የሚያደናቅፍ፤ እንዲሁም በሕዝቦች

መካከል መኖር የሚገባውን ሰላምና መረጋጋት የሚያደፈርስ ከመሆኑም በላይ በአንድ ሀገር ውስጥ የሚኖሩ ዜጎች አንድነት የሚቃረን መሆኑን በማረጋገጥ፤

የዘር ገደብ ከሁሉም የሰው ልጅ እሴቶች ጋር እንደሚቃረን በማመን፤

እስካሁን ድረስ በግልጽና በተጨባጭ የሚንጸባረቁትንና በአንዳንድ የዓለም አካባቢዎችና የመንግሥት ፖሊሲዎች የሚታዩት በዘር የበላይነት ወይም ጥላቻ የተመሰረቱ እንደ የአፓርታይድ ፖሊሲዎች፣ አድልዎና ማበላለጥ የመሳሰሉት የዘር ልዩነቶች አሳሳቢ መሆናቸውን በመረዳት፤

ሁሉም የዘር ልዩነት ዓይነቶችና መገለጫዎች በአስቸኳይ ለማስወገድ የሚያስችሉ ተገቢ እርምጃዎች መውሰድና የዘር ልዩነት መርሆዎችና ተግባሮች በመዋጋት በሰው ልጅ ዘሮች መካከል መግባባት የሰፈነበት፤ ከማንኛውም ዓይነት የዘር ልዩነትና አድልዎ ነጻ የሆነ የዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ ለመገንባት ያለው ዝግጁነት በመግለጽ፤

የዓለም አቀፍ የሥራ ድርጅት እ.ኤ.አ. በ1958 ባወጣው በሥራና በሥራ ቅጥር ሂደት የሚያጋጥም ልዩነት የሚመለከት ቃል ኪዳን እና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ተቋም እ.ኤ.አ. በ1960 ያወጣው በትምህርት የሚያጋጥም ልዩነት የሚያስወግድ ቃል ኪዳን ግምት ውስጥ በማስገባት፤

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሁሉም ዓይነት የዘር ልዩነቶች ለማስወገድ ባወጣው መግለጫ የሰፈሩት መርሆዎችን ለመተግበርና አስቀድሞ በማጽደቅ አስፈላጊ ተግባራዊ እርምጃ ለመውሰድ እንደሚከተለው ተስማምተዋል፡፡

# ክፍል አንድ

## አንቀጽ 1

1. በዚህ ስምምነት “**የዘር ልዩነት**” ማለት ማንኛውም ዓይነት አድልዎ፣ ማግለል፣ መገደብ ወይም ማስበለጥ ወይም በዘር፣ በቀለም፣ በትውልድ፣ በብሔር ወይም በዘር ሃረግ በመመስረት የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ፣ የባህላዊ ወይም በማንኛውም የሕብረተሰብ የኑሮ መስክ ያሉት ሰብአዊ መብቶችና መሰረታዊ ነጻነቶች በእኩልነት የማግኘትና የመጠቀም ዕድል የመፃረር ዓላማ ያለው ተግባር ይገልፃል፡፡
2. ይህ ስምምነት በዜጎችና ዜጎች ባልሆኑ ሰዎች መካከል አድልዎ፣ ማግለል ወይም ገደብ ባስቀመጠ የቃል ኪዳኑ ፈራሚ በሆነ ሀገር ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡
3. የዚህ ስምምነት አንቀጾች የስምምነቱ ፈራሚ የሆኑ ሀገራት ሀገራዊ ማንነትና በትውልድ ወይም በሕግ ዜግነት ማግኘት በሚመለከት ለሚያወጧቸው ሕጎች በሚቃረን መልኩ በፍፁም አይተረጎሙም፡፡ ይህ የሚሆነው ግን ሀገራቱ የሚያወጧቸው ሕጎች የአንዱን ወገን ዜግነት የማግለል ዓላማ የሌላቸው ከሆኑ ነው፡፡
4. አንድ የተወሰነ ዘር ወይም የጎሳ ስብስብ ወይም ግለሰቦች ሰብአዊ መብቶቻቸው እና መሰረታዊ ነጻነታቸው በእኩልነት እንዲያገኙ በማቀድ ብቻ ለእነኝህ የጎሳ ስብስብ ወይም ግለሰቦች ተብሎ የሚደረግ ልዩ ድጋፍ እንደ የዘር ልዩነት አይወሰድም፤ ይሁን እንጂ ይህ ልዩ ድጋፍ ለተለያዩ የጎሳ ስብስብ የተለያዩ መብቶች በሚያጎናፅፍ መልኩ መተግበር የለበትም ብቻ ሳይሆን፤ ይህ ልዩ ድጋፍ የታለመለትን ግብ ከመታ በኋላ መቆም አለበት፡፡

## አንቀጽ 2

1. ይህን ስምምነት የተቀበሉ ሀገራት የዘር ልዩነት በማውገዝ በማንኛው መልኩ የሚገለጽ የዘር ልዩነት ማስወገድ የሚያስችል ፖሊሲ በተቻለ መጠንና በአስቸኳይ በመንደፍ በሰው ልጅ ዘሮች መካከል መቻቻል ለማስፈን፤

   ሀ/ ይህንን ስምምነት የተቀበሉ ሀገራት በሰዎች፣ በሰዎች ስብስብ ወይም ተቋሞች መካከል ልዩነት የሚፈጥር እርምጃ አይወሰዱም ወይም ተግባር አያካሂዱም፤ የሀገራቸው ወይም ግዛታቸው መንግሥታዊ ባለሥልጣናት እና መንግሥታዊ ተቋማት ቃል ኪዳኑን የሚፃረር ተግባር አይፈጽሙም፤

   ለ/ ይህንን ስምምነት የተቀበሉ ሀገራት የዘር ልዩነት የሚያካሂዱ ሰዎችን ወይም ተቋማትን አይደግፉም፤ አይረዱም ወይም ከለላ አይሰጡም፡፡

ሐ/ ይህንን ስምምነት የተቀበሉ ሀገራት መንግሥታዊ፣ ሀገራዊ ወይም አካባቢያዊ ፖሊሲዎች ለማስተካከል፤ እንዲሁም የዘር ልዩነት የሚፈጥሩና የሚያስፋፉ ሕጎችና መመሪያዎች ለማሻሻል፣ ለመሰረዝ ወይም ለመሻር የሚያግዙ ተገቢ እርምጃዎች መውሰድ አለባቸው፤

መ/ ይህንን ስምምነት የተቀበሉ ሀገራት በሰዎች፣ በቡድኖች ወይም በተቋሞች የሚካሄድ የዘር ልዩነት ለመግታትና ለማስወገድ ማንኛውም ዓይነት ጥረት ማካሄድ አለባቸው። አስፈላጊ ሆኖ በተገኘበት ወቅትም ሕግ ማውጣት አለባቸው፤

ሠ/ ይህንን ስምምነት የተቀበሉ ሀገራት አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ውሁድ ብዝሃ ዘር የያዙ ድርጅቶችና እንስቃሴዎች ለማበረታታት፤ እንዲሁም በሰው ልጅ ዘሮች መካከል የሚፈጠሩ አጥሮች ለማስወገድና የዘር ልዩነት ለማስቀረት የተለያዩ ጥረቶች ያካሂዳሉ።

2. ይህንን ስምምነት የተቀበሉ ሀገራት በግዛታቸው ውስጥ የሚኖሩ ጎሳዎች እና ግለሰቦች ሰብአዊ መብቶቻቸውና መሰረታዊ ነጻነታቸው በተሟላ መንገድና በእኩልነት እንዲጠቀሙ የማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ እና ሌሎች ጥቅሞቻቸውና እድገታቸው የሚያረጋግጡ የተለዩና ተጨባጭ እርምጃዎች መውሰድ አለባቸው። እነዚህ እርምጃዎች ለተለያዩ ጎሳዎች እኩል ያልሆኑ እና የተለያዩ መብቶች የሚያጎናፅፉ መሆን የለባቸውም። እንዲሁም መነሻ ያደረጉት ዓላማ ግቡን ከመታ በኋላ ማቋረጥ አለባቸው።

## አንቀጽ 3

ይህንን ስምምነት የተቀበሉ ሀገራት በተለይም የዘር አድልዎና አፓርታይድ እንዲያወግዙና የዘር ልዩነት የሚያስከትል ተግባርና ባሕርይ በግዛታቸው ውስጥ እንዳይንሰራፉ መከላከል፣ መግታትና ማስወገድ አለባቸው።

## አንቀጽ 4

ይህንን ስምምነት የተቀበሉ ሀገራት የአንድ ጎሳ ወይም የሰዎች ስብስብ የቀለም ወይም ብሔራዊ አመጣጥን የበላይነት የሚሰብክ ወይም በማንኛውም መልኩ የዘር ጥላቻና ልዩነት የሚያራምድ ፕሮፓጋንዳና ተቋም ማውዝ አለባቸው። እንዲህ ዓይነቱን ቅስቀሳና ተግባር የሚያስወግዱ ገንቢ ሕጎች በአስቸኳይ በማርቀቅ ከሰብአዊ መብቶች ዓለም አቀፋዊ መግለጫ እና በዚሁ ስምምነት አንቀጽ 5 ከሰፈሩት መብቶች ጋር የተሳሰሩ ደንቦች መንደፍ አለባቸው። ከሚቀረፁት ደንቦች መካከል፤

ሀ/ በዘር የበላይነት እና ጥላቻ ላይ በመመስረት የሚሠራጭ ቅስቀሳና በዘር ልዩነት የሚመሰረት ማነሳሳት በሕግ የሚያስቀጣ ወንጀል መሆኑን የሚገልፅ ሕግ መደንገግ፤ እንዲሁም የማንኛውም ዘር ወይም የሰዎች ስብስብ ቀለም ወይም ብሔራዊ ምንጭ የሚፃረር ተግባርና ዓመፅ ወይም

ማነሳሳት የሚቃወም፣ ዘረኛ እንቅስቃሴዎችን መደገፍና የገንዘብ ዕርዳታ ማድረግ ወንጀል መሆኑን የሚያስገነዝብ ሕግ መቅረፅ፤

ለ/ የዘር ልዩነት የሚያራምዱና የሚያነሳሱ፤ እንዲሁም የተደራጁና ማንኛውም ዓይነት የዘር ፕሮፓጋንዳ የሚያስፋፉ ተቋሞች ማገድና ሕገ ወጥ መሆናቸውን ማወጅ፣ በእንደዚህ ዓይነቶቹ ተቋሞችና እንቅስቃሴዎች ተሳታፊ መሆን በሕግ የሚያስቀጣ ወንጀል መሆኑን ዕውቅና መስጠት አለባቸው፡፡

ሐ/ የመንግሥት ባለሥልጣናት ወይም የመንግሥት ተቋሞች የዘር ልዩነት እንዲያራምዱና እንዲያነሳሱ መፍቀድ የለባቸውም፡፡

## አንቀጽ 5

በዚሁ ስምምነት አንቀጽ 2 ከሰፈሩት መሰረታዊ ግዴታዎች በተጣጣመ መልኩ ይህንን ስምምነት የተቀበሉ ሀገራት ማንኛውም ዓይነት የዘር ልዩነት ለመከላከልና ለማስወገድ፤ እንዲሁም የዘር፣ የቀለም፣ የብሔር ወይም የትውልድ ሃረግ ማበላለጥ ሳይደረግበት ማንኛውም ሰው በሕግ ፊት በእኩልነት የሚታይበት ሁኔታ ለመፍጠርና የሚከተሉት መብቶች እንዲጎናፀፍ ተገቢ እርምጃ ይወስዳሉ፡፡

ሀ/ በዳኝነት ተቋማት እና በማንኛውም የፍትሕ አስተዳደር አካላት ፊት በእኩልነት የመስተናገድ መብት፤

ለ/ ከመንግሥት ባለሥልጣን፣ ከግለሰብ፣ ከሰዎች ስብስብና ከተቋም ለሚደርስ ጥቃትና የአካል ጉዳት የመንግሥት ጥበቃ የማግኘትና የግል ጸጥታ የማግኘት መብት፤

ሐ/ ፖለቲካዊ መብት በተለይ ደግሞ ሁሉ አቀፍና እኩል ተሳትፎ በሚያረጋግጡ ምርጫዎች በመራጭነትና ተመራጭነት የመሳተፍ መብት፣ በሁሉም የመንግሥት አስተዳደር ደረጃዎች የመሳተፍና በሁሉም ደረጃ በሚገኙ ሕዝባዊ ጉዳዮች እኩል አገልግሎት የማግኘት መብት፤

መ/ ሌሎች የሲቪል መብቶች፤ በተለይም፡-

i. በሀገሩ የግዛት ክልል ውስጥ በነጻነት የመንቀሳቀስና የመኖር መብት፤

ii. ከየትኛውም ሀገር፣ ከራስ ሀገርም ጭምር ለቆ ለመውጣትና ወደ ራስ ሀገር ተመልሶ የመግባት መብት፤

iii. ዜግነት የማግኘት መብት፤

iv. የማግባትና የትዳር ጓደኛውን ሰው የመምረጥ መብት፤

v. በግል ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን ንብረት የማፍራት መብት፤

vi. የውርስ መብት፤

vii. የማሰብ፣ የኅሊናና የሃይማኖት ነጻነት መብት፤

viii. የራስ አመለካከት የመያዝና የመግለጽ መብት፤

ix. ሰላማዊ ስብሰብ የማካሄድና የመደራጀት ነጻነት መብት፤

ሠ/ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ መብቶች፤ በተለይም፡-

i. የመሥራት፣ በነጻ ፍላጎት የመቀጠር፣ ፍትሐዊና አመቺ የሥራ ሁኔታ እና የሥራ ዋስትና የማግኘት፣ ለእኩል ሥራ እኩል ክፍያ የማግኘት፤ እንዲሁም ፍትሐዊና ተመጣጣኝ ክፍያ የማግኘት መብቶች፤

ii. የሠራተኛ ማኅበራት የማቋቋምና የመደራጀት መብት፤

iii. የመኖሪያ ቤት የማግኘት መብት፤

iv. መንግሥታዊ የሕክምና አገልግሎት፣ የጤና እንክብካቤ ማኅበራዊ ዋስትና እና ማኅበራዊ አገልግሎት የማግኘት መብት፤

v. ትምህርትና ስልጠና የማግኘት መብት፤

vi. በባህላዊ እንቅስቃሴዎች በእኩልነት የመሳተፍ መብት፤

ረ/ መጓጓዣ፣ ሆቴል፣ ምግብ ቤት፣ ቡና ቤት፣ ትያትር ቤት፣ የመናፈሻ ቦታ በመሳሰሉት ሕዝብን ለማገልገል የተቋቋሙ አገልግሎት ሰጪዎች ከሚሰጡት አገልግሎት በእኩልነት የመጠቀም መብት፤

## አንቀጽ 6

ይህንን ስምምነት የተቀበሉ ሀገራት ስምምነቱን የሚቃረን ሰብአዊ መብቶችንና መሰረታዊ ነጻነቶችን የሚጋፋ ማንኛውም የዘር ልዩነት ተግባር ለመመከት የሚያስችሏቸው ብሔራዊ የዳኝነት ተቋሞች ሌሎች የመንግሥት ተቋማት በመጠቀም በግዛታቸው ክልል ውስጥ የማንኛውም ሰው ዋስትና ለማረጋገጥ የሚያስችላቸው ሥርዓት መዘርጋት አለባቸው። ከዚህ በተጨማሪ በደረሰው ጉዳትና መድልዎ መጠን ከችሎቶቹ ፍትሐዊና በቂ ካሳ የማግኘት መብት መረጋገጥ አለበት።

## አንቀጽ 7

ይህንን ስምምነት የተቀበሉ ሀገራት ወደ ዘር መድልዎ የሚያመሩ የተሳሳቱ አመለካከቶችን ለመመከት ብሎም በሀገራት ወይም የዘርና የጎሳ ስብስቦች መካከል መቻቻልንና ወዳጅነትን ለማስፈን እና የተባበሩት መንግሥታት ቻርተር፣ ዓለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች መግለጫና ሁሉንም ዓይነት የዘር

መድልዎችን ለማስወገድ የወጣው የተባበሩት መንግሥታት መግለጫና የዚህ ስምምነት ዓላማዎችንና መርሆዎችን ለማራመድ፤ በተለይም በትምህርት፣ ባህልና መረጃ መስኮች አፋጣኝና ውጤታማ እርምጃዎችን ይወስዳሉ፡፡

## ክፍል ሁለት

## አንቀጽ 8

1. በዘር ላይ የተመሰረተ መድልዎን ለማስወገድ የሚሰራ ከዚህ በኋላ ኮሚቴው ተብሎ የሚጠቀስ ኮሚቴ ይቋቋማል። ይህ ኮሚቴ የስምምነቱ ፈራሚ ከሆኑት ሀገራት ዜጎች መካከል በሀገራቱ የሚመረጡ፣ በከፍተኛ ሥነ ምግባርና ገለልተኛነት የሚታወቁ 18 ባለሙያዎችን ያቅፋል። እነኝህ አባላት ራሳቸውን በመወከል በግል የሚያገለግሉ ሲሆን፤ በሚመረጡበት ወቅትም ጂኦግራፊያዊ ስብጥርና የተለያየ የሥልጣኔ፤ እንዲሁም ዋና ዋና የሕግ ሥርዓቶችን የሚወክሉ መሆናቸውን ግምት ውስጥ ይገባል።

2. የኮሚቴው አባላት ስምምነቱን ከተቀበሉ ሀገራት ከቀረቡ ዕጩዎች መሃል በምስጢራዊ የምርጫ ሥርዓት ይመረጣሉ፡ እያንዳንዱ ይህንን ቃል ኪዳን የተቀበለ ሀገር ከዜጎቹ መካከል አንድ መጠቆም ይችላል።

3. የመጀመሪያው ምርጫ ስምምነቱ ከጸናበት ቀን ጀምሮ ከስድስት ወራት በኋላ ይካሄዳል። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ለእያንዳንዱ ምርጫ ቢያንስ ሦስት ወር ሲቀረው የሚመለከታቸው የስምምነቱ አባል ሀገራት በሁለት ወር ውስጥ ዕጩዎቻቸውን እንዲገልፁ በደብዳቤ ይጠይቃቸዋል። ዋና ጸሐፊው የዕጩዎች ስም ዝርዝር በፊደል ቅደም ተከተል በማዘጋጀት የተወከሉበት ሀገር ጨምሮ በመጥቀስ ስምምነቱን ለተቀበሉ ሀገራት ያሳውቃል።

4. ዋና ጸሐፊው በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጽሕፈት ቤት በሚጠራው የስምምነቱ አባል ሀገራት ስብሰባ የኮሚቴው አባላት ምርጫ ይካሄዳል፡ የስምምነቱ ፈራሚ ከሆኑት ሀገራት መካከል ሁለት ሦስተኛ በስብሰበው ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል። የኮሚቴው አባላት ሆነው የሚመረጡትም በስብሰባው በመገኘት ድምፅ ከሰጡት የስምምነቱ ፈራሚ ሀገራት ከፍተኛው እና ፍፁም አብላጫ ድምፅ ያገኙት ይሆናሉ።

5. ሀ/ የኮሚቴው አባላት ለአራት ዓመታት የሥራ ጊዜ ያገለግላሉ። በመጀመሪያ ምርጫ ከተመረጡት ውስጥ የዘጠኙ አባላት የሥራ ጊዜ ግን ሁለት ዓመት ብቻ ይሆናል። የመጀመሪያ ምርጫ እንደተካሄደ የዘጠኙ የኮሚቴው አባላት ማንነት የኮሚቴው ሊቀመንበር በሚያወጣው ዕጣ ይለያል፡

   ለ/ ከኮሚቴው አባላት ሰው ሲጓደል፣ በዕጩነት ያቀረበው አባል ሀገር ከዜጎቹ መካከል አንድ ባለሞያ መርጦ ይመድባል። ይህ ምደባ የሚፀናው ኮሚቴው ከተቀበለው ነው።

6. ይህንን ስምምነት የተቀበሉ ሀገራት፣ የኮሚቴው አባላት በኮሚቴው የተሰጣቸውን የሥራ ኃላፊነት በሚያከናውኑበት ወቅት የሚያስፈልጋቸውን ወጪ የመሸፈን ግዴታ አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 9

1. ይህንን ስምምነት የተቀበሉ ሀገራት የስምምነቱን አፈጻጸም በሚመለከት የወሰዷቸውን ሕግ የማውጣት፣ የሚሰጡት የዳኝነት፣ የአስተዳደር ወይም ሌሎች እርምጃዎች የሚገልጽ ዘገባ በኮሚቴው እንዲታይ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ያቀርባሉ፡፡ ይህንን የሚፈጽሙትም፡-
   ሀ/ ስምምነቱ ለሚመለከተው ሀገር አስገዳጅ መሆን ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ፤
   ለ/ ከዚያ በኋላ የሚቀርቡ ዘገባዎች በየሁለት ዓመትና ኮሚቴው ዘገባ እንዲቀርብለት በሚጠይቅበት ጊዜ ይሆናል፡፡ ቃል ኪዳኑ የተቀበሉ ሀገራት ተጨማሪ መረጃ እንዲያቀርቡ ኮሚቴው ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ኮሚቴው የሥራ እንቅስቃሴውን የሚዳስስ ዘገባ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ አማካኝነት በየዓመቱ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፡፡ በሪፖርቱ ስምምነቱን ከተቀበሉ ሀገራት ያገኘው መረጃና ሪፖርት በመመርመር የራሱ አስተያየትና የመትፍሔ ሃሳብ ሊያካትት ይችላል፡፡ አስተያየቶችና አጠቃላይ የመፍትሔ ሃሳቦች፣ የስምምነቱ ፈራሚ ሀገራት የሰጡት አስተያየት ካለም በማከል ነው ለጠቅላላ ጉባኤው የሚቀርቡት፡፡

## አንቀጽ 10

1. የኮሚቴው የራሱን የሥነ ሥርዓት ሕግ ያወጣል፡፡
2. ኮሚቴው ለሁለት ዓመት የሚያገለግሉ ሥራ አስፈጻሚዎች ይመርጣል፡፡
3. ለኮሚቴው አስፈላጊ የሆነ አገልግሎት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ጽሕፈት ቤት ያቀርብለታል፡፡
4. በመደበኛነት የኮሚቴው ስብሰባዎች በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጽሕፈት ቤት ይካሄዳሉ፡፡

## አንቀጽ 11

1. ይህንን ስምምነት የተቀበለ አንድ ሀገር ስምምነቱን የተቀበለ ሌላ ሀገር የስምምነቱን ድንጋጌዎች ተግባራዊ አላደረገም የሚል እምነት ከያዘ ጉዳዩን ለኮሚቴው ማቅረብ ይችላል፡፡ ኮሚቴው በበኩሉ የቀረበለትን ቅሬታ ለሚመለከተው ሀገር ያስተላልፋል፡፡ ተቀባዩ ሀገርም ቅሬታው

ከደረሰው ጊዜ ጀምሮ በሦስት ወራት ውስጥ ጉዳዩን የሚያብራራና የተወሰደ የማስተካከያ እርምጃ ካለም በጽሑፍ ለኮሚቴው ያሳውቃል፡፡

2. የመጀመሪያው ቅሬታ የስምምነቱን ድንጋጌዎች አላከበረም ለተባለው ሀገር ከደረሰ ከቀረበ በኋላ በስድስት ወራት ውስጥ በሁለትዮሽ ድርድር ወይም በሌላ ሥነ ሥርዓት ሁለቱን ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሀገራት የሚያግባባ መፍትሔ ካልተገኘ ከሁለቱም አንዱ ጉዳዩን በድጋሚ ወደ ኮሚቴው የማቅረብና ስለጉዳዩ ለሌላኛው ሀገር የማሳወቅ መብት አለው፡፡
3. ኮሚቴው በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት በቀረበለት ጉዳይ ላይ ውሳኔ የሚሰጠው፣ የሚመለከተው ሀገር የዓለም አቀፍ ሕግ መርሆዎች በመከተልና ሁሉንም የመፍትሔ አገባቦች በመጠቀም ለጉዳዩ ዕልባት ለመስጠት አለመቻሉን ካረጋገጠ በኋላ ነው፡፡ መፍትሔ ለመስጠት የሚወስደው ጊዜ በአዕምሮ ግምት ረጅም የሚባል ጊዜ ከሆነ ሕጉ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡
4. ኮሚቴው የቀረበለት ቅሬታ በሚመለከት ስምምነቱን የተቀበሉ የሚመለከታቸው ሀገራት አስፈላጊነት ያለው ተጨማሪ መረጃ እንዲያቀርቡ ጥሪ ያቀርባል፡፡
5. በዚሁ አንቀጽ የተመለከቱ ጉዳዮች በኮሚቴው በሚታዩበት ወቅት ስምምነቱን የተቀበሉና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሀገራት በኮሚቴው ስብሰባዎች ድምፅ የመስጠት መብት ሳይኖራቸው የሚሳተፉ ተወካዮች የመላክና የማጣራቱን ሂደት እንዲከታተሉ የማድረግ መብት አላቸው፡፡

## አንቀጽ 12

1. ሀ/ ኮሚቴው አስፈላጊ ናቸው ያላቸው መረጃዎች ከያዘና ካመሳከረ በኋላ ሊቀመንበሩ የኮሚቴው አባላት የሆኑ ወይም ያልሆኑ አምስት ሰዎችን በአባልነት የያዘ (ከዚህ በኋላ ኮሚሽን በማለት የሚጠቀስ) ጊዜያዊ የሽምግልና ኮሚሽን ይሰይማል፡፡ የኮሚሽኑ አባላት ስምምነቱን በተቀበሉ ባለጉዳይ የሆኑ ሀገራት ሙሉ ፈቃድ የሚሰየሙ ይሆናሉ፡፡ ኮሚሽኑ በዚሁ ስምምነት በሰፈሩት መርሆዎች በመመስረት ለጉዳዩ መፍትሔ ለመስጠት በማቀድ ባለ ጉዳይ ለሆኑት ሀገራት አገልግሎቱን ይሰጣል፡፡

   ለ/ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሀገራት በሁሉም ወይም በከፊል የኮሚሽኑ አባላት ምርጫ በሦስት ወራት ውስጥ ካልተስማሙ፣ ኮሚቴው ከራሱ አባላት ውስጥ በምስጢራዊ የምርጫ አካሄድ በሚያካሂደው ምርጫ የሁለት ሦስተኛው ድምፅ ያገኙ ሰዎች የኮሚሽኑ አባላት ሆነው እንዲሰሩ ያደርጋል፡፡
2. የኮሚሽኑ አባላት ራሳቸውን በመወከል ሥራቸውን ያከናውናሉ፡፡ የባለጉዳይ ሀገራት ዜጎች መሆን የለባቸውም፤ በተጨማሪም ስምምነቱን ያልፈረሙ ሀገራት ዜጎች መሆን የለባቸውም፡፡
3. ኮሚሽኑ የራሱ ሊቀ መንበር ይመርጣል፤ የሚመራበት የሥነ ሥርዓት ደንብ ያወጣል፡፡
4. የኮሚሽኑ ስብሰባ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጽሕፈት ቤት ወይም ኮሚሽኑ በሚወስነው ሌላ ተስማሚ ቦታ ይካሄዳል፡፡

5. በዚሁ ስምምነት አንቀጽ 10 መሰረት የሚሰጠው የጽሕፈት ቤት አገልግሎት የስምምነቱ ፈራሚ በሆኑት ሀገራት መካከል ያለመስማማት ሲሆን ጉዳዩን ለመመርመር ለሚሰየመው ኮሚሽንም አገልግሎት ይሰጣል፡፡
6. የጉዳዩ ባለቤት የሆኑ ሀገራት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ በሚያቀርብባቸው ግምት መሰረት ሁሉንም የኮሚሽኑን ወጪዎች እኩል ይከፍላሉ፡፡
7. አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሰረት የጉዳዩ ባለቤትና የስምምነቱ ፈራሚ የሆኑ ሀገራት የወጣውን ወጪ እስከሚተኩ ድረስ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ የኮሚሽኑ አባላት ወጪ የመሸፈን ሥልጣን አለው፡፡
8. ለኮሚቴው የደረሰውና በራሱ መንገድ ያጠናቀረው መረጃ ለኮሚሽኑ ይቀርባል፡፡ በተጨማሪም ኮሚሽኑም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሀገራት ሌላ ተጨማሪ መረጃ እንዲያቀርቡ ጥሪ ማቅረብ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 13

1. ኮሚሽኑ ጉዳዩን ሙሉ በሙሉ ከመረመረ በኂላ ከክስ አቅራቢዎች ጉዳይ ጋር ግንኙነት ባላቸው የፍሬ ነገር ጭብጦች ላይ ራሱ የደረሰበትን ድምዳሜና ውዝግቡን ለመፍታት የሚጠቅሙ አግባብነት ያላቸው የመፍትሔ ሃሳቦችን ያካተተ ዘገባ በማዘጋጀት ለኮሚቴው ሊቀመንበር ያቀርባል፡፡
2. የኮሚቴው ሊቀመንበር ከኮሚሽኑ የደረሰውን ዘገባ ባለጉዳይ ለሆኑ ሀገራት ለእያንዳንዳቸው ያስተላልፋል፡፡ ሀገራቱም በኮሚሽኑ ዘገባ የተቀመጡትን የመፍትሔ ሃሳቦች መቀበላቸውንና አለመቀበላቸውን በሦስት ወራት ውስጥ ለኮሚቴው ሊቀመንበር ማሳወቅ አለባቸው፡፡
3. በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 ከተጠቀሰው ጊዜ በኂላ የኮሚቴው ሊቀመንበር የኮሚሽኑ ዘገባና የተወዛጋቢ ሀገራት መግለጫን በማጣመር ይህንን ስምምነት ለተቀበሉ ሀገራት ያስተላልፋል፡፡

## አንቀጽ 14

1. ይህንን ስምምነት በተቀበለ ሀገር ግዛት ክልል ውስጥ በዚሁ ስምምነት የሰፈሩ መብቶቻችን ተጥሰዋል በማለት ከግለሰቦች ወይም ከቡድኖች የሚቀርብ ክስ ኮሚቴው ተቀብሎ የመመርመር ሥልጣን እንዳለው ስምምነቱን የተቀበለ ሀገር በማንኛውም ጊዜ መግለጽ ይችላል፡፡ ይህንን እውቅና ባልሰጠ ሀገር የሚቀርብ ክስ በኮሚቴው አይመረመርም፡፡
2. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተገለጸው መሰረት እውቅና የሰጠ ሀገር በግዛቱ ክልል ከሚገኙ ግለሰቦችና ቡድኖች የሚቀርቡ በዚሁ ስምምነት የሰፈሩ መብቶቻችን ተጥሰዋል የሚሉትን ክሶች የሚመረመር ብቃት ያለው ሀገራዊ ተቋም ማቋቋም ይችላል፡፡ ሕጋዊ ተቋሙ በሁሉም አካባቢያዊ መፍትሔዎች መቋጫ ያላገኙ ጉዳዮችን ይመረምራል፡፡

3. በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚሰጥ እውቅና እና በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት የሚቋቋም ተቋም የሚመለከት ሰነድ ጉዳዩ የሚመለከተውና የስምምነቱ አባል የሆነ ሀገር ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ እንዲደርስ ያደርጋል፡፡ ዋና ጸሐፊውም የዚሁ ሰነድ ቅጂዎች የስምምነቱ ፈራሚ ለሆኑት ሀገራት እንዲደርስ ያደርጋል፡፡
4. የተመዘገበው ክስ በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት ከሚቋቋመው አካል ጋር ይቀመጣል፤ የክሱ የተረጋገጡ ቅጂዎች አግባብ ባለው አሰራር ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ በየዓመቱ ይላካሉ፡፡ የክሶች ይዘት ግን ይፋ አይደረጉም፡፡
5. በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 የተቋቋመው አካል የሚሰጠው የመፍትሔ ሃሳብ በቂ ነው ብሎ ካላመነ ክስ አቅራቢው በስድስት ወራት ውስጥ ለኮሚቴው ማመልከቻ የማቅረብ መብት አለው፡፡
6. ሀ/ ኮሚቴው የቀረበለትን ክስ የስምምነቱን ሕጎች ጥሷል በማለት ክስ የቀረበበት ሀገር እንዲያውቀው ይልክለታል፡፡ ይሁን እንጂ ክስ ያቀረበው ግለሰብ ወይም ቡድን ካልፈቀደ ማንነቱ አይገልጽም፡፡ ይህ እንተደተጠበቀ ሆኖ ኮሚቴው የከሳሽ ስም የሌለበት ክስ አይቀበልም፡፡
   ለ/ ተቀባዩ ሀገር ጉዳዩን የሚያብራራ ወይም ለጉዳዩ የተሰጠ መፍትሔ ካለ የሚገልጽ ጽሑፍ በሦስት ወራት ውስጥ ለኮሚቴው ያቀርባል፡፡
7. ሀ/ ኮሚቴው ስምምነቱን ከተቀበለ ተከሳሽ ሀገርና ከከሳሽ በቀረቡለት መረጃዎች በመመስረት የማጣራት ግንኙነት ያካሂዳል፡፡ ከሳሹ በሀገሩ ውስጥ የሚገኙት ሁሉም የክስ አቀራረብ ደረጃዎች ሳይጠቀም ክሱን ለኮሚቴው ካቀረበ ኮሚቴው ጉዳዩን አይቀበልም፡፡ ይሁን እንጂ የመፍትሔው ሂደት በአዕምሮ ግምት ረጅም ጊዜ ከወሰደ ይህ ሕግ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡
   ለ/ ኮሚቴው በጉዳዩ አስተያየትና የመፍትሔ ሃሳቦች ካለው ለተከሳሹ ሀገርና ለከሳሹ ያቀርባል፡፡
8. ኮሚቴው ባደረገው ጉዳዩን የማጣራት ግንኙነት ያገኘው ጭማቂ ሃሳብ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም ክስ የቀረበበት ሀገር የሰጠው ማብራሪያና መግለጫ፤ እንዲሁም የራሱ አስተያየትና የመፍትሔ ሃሳቦች ያካተተ ጽሑፍ በሚያቀርበው ዓመታዊ ዘገባ ያካትታል፡፡
9. ኮሚቴው በዚሁ አንቀጽ የተመለከቱ ተግባራትን ማከናወን የሚችለው በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ስምምነቱን ከተቀበሉ ሀገራት መካከል ቢያንስ አስሩ እውቅና ከሰጡት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 15

1. እ.አ.አ. ዲሴምበር 10 ቀን 1960 በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አጠቃላይ ጉባኤ ውሳኔ ቁጥር 1514 (XV) የተደነገገውና በቅኝ ግዛት ስር የሚገኙት ሀገራትና ሕዝቦች ነጻነት ያቀዳጀው መግለጫ ተግባራዊነት እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በዚሁ የሰፈሩ ሕጎች እነኝህ ሕዝቦች በሌላ የዓለም አቀፍ አሰራር ወይም ልዩ ተልዕኮ ባላቸው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አካላት የተጎናፀፉት ክስ የማቅረብ መብት በማንኛውም መንገድ አይገደብም፡፡

2. ሀ/ በዚሁ ስምምነት አንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚቋቋመው ኮሚቴ የአጠቃላዩ ጉባኤ ውሳኔ 1514 (XV) ተግባር ላይ በሚውልባቸው በሞግዚታዊ እና ራስ ገዝ ባልሆነ መስተዳድር የሚተዳደሩ ነዋሪያዎች የሚያቀርቡት ክስ ቅጂ ይቀበላል። ይህንን ክስ ለመመርመርና በዚሁ ስምምነት የሰፈሩት መርሆዎችና ግቦች በቀጥታ ለመፈጸም ለሚቋቋሙ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አካላት በክሱ ያለውን አስተያየትና የመፍትሔ ሃሳቦች ያቀርባል።
   ለ/ ኮሚቴው በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (ሀ) የተጠቀሱት ግዛቶች ለማስተዳደር የሚሰየሙት ጉዳዩን የሚመለከታቸው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አካላት ከቃል ኪዳኑ ዓላማ ጋር ትብብር ያለው የሕግ አውጪ፣ ፍርድ ቤት፣ አስተዳደራዊ ሌሎች ተግባራት በሚመለከት የሚያዘጋጁትን ዘገባ ቅጂ ይቀበላል፡
3. ኮሚቴው ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አጠቃላይ ጉባኤ በሚያቀርበው ዘገባ ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የተለያዩ አካላት የተቀበለው ክስና ዘገባ፤ እንዲሁም ኮሚቴው በክሱና ዘገባው በመመስረት የሚሰጠው አስተያየት፣ መግለጫና የመፍትሔ ሃሳብ ያካትታል።
4. ኮሚቴው ለስምምነቱ ግቦች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችና በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 (ሀ) ከተጠቀሱት ግዛቶች ትስስር ያላቸው ጉዳዮች በማስመልከት ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ መጠየቅ ይችላል።

## አንቀጽ 16

የዚሁ ስምምነት አንቀጾች ከአድልዎና ልዩነት ተያያዥነት ያላቸው ውዝግቦችና ክሶች መፍትሔ ለመስጠት ከሚወጡት ሌሎች ሥነ ሥርዓቶች በማይቃረን መልኩ ተግባራዊ ይሆናሉ። ልዩ ተልዕኮ የተሰጣቸው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አካላት ከሚያወጡት ሥነ ሥርዓት ስምምነቱን የተቀበሉ ሀገራት ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሰረት በማድረግ ግጭት ለመፍታት ከሚደነግጓቸው ሥነ ሥርዓቶችም አይቃረኑም።

# ክፍል ሦስት

## አንቀጽ 17

1. ይህ ስምምነት፤ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና ልዩ ተልዕኮ የተሰጣቸው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አካላት አባል የሆነ የዓለም አቀፍ ፍትሕ ፍርድ ቤት የተመሰረተበት ሕግ የተቀበለ ወይም በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አጠቃላይ ጉባኤ ይህንን ስምምነት እንዲቀበል ጥሪ የቀረበለት ማንኛውም ሀገር እንዲፈርምበት ክፍት ነው።
2. ይህ ስምምነት ተፈጻሚ የሚሆነው በፈራሚ ሀገራት ሲጸድቅ ነው። የማጽደቂያ ሰነዶቹም በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ጽ/ቤት ይቀመጣሉ።

## አንቀጽ 18

1. ይህ ስምምነት በአንቀጽ 17 ንኡስ አንቀጽ 1 የተጠቀሱት ሀገራት እንዲቀበሉት ክፍት ነው፡፡
2. የመቀበያ ሰነዶችም ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ መቅረብ አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 19

1. የስምምነቱ ሃያ ሦስተኛው የማጽደቂያ ወይም የመቀበያ ሰነድ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ በሰላሳኛው ቀን ስምምነቱ የጸና ይሆናል፡፡
2. የስምምነቱ ሃያ ሰባተኛው የማጽደቂያ ወይም የመቀበያ ሰነድ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ከቀረበ በኂላ ስምምነቱን የሚያጸድቁ ሀገራት የየራሳቸው የማጽደቂያ ወይም የመቀበያ ሰነድ ከአቀረቡበት ጊዜ ጀምሮ በሰላሳኛው ቀን በስምምነቱ ይገደዳሉ፡፡

## አንቀጽ 20

1. የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ስምምነቱን የሚቀበሉ ሀገራት ስምምነቱን ሲያጸድቁ ወይም ሲቀበሉ ያስመዘገቡት ተአቅቦ ለሌሎች የስምምነቱ ፈራሚ ሀገራት ያሳውቃል፡፡ ተአቅቦውን የሚቃወም ማንኛውም ሀገር መልእክቱ ከደረሰው በኂላ በዘጠና ቀናት ውስጥ እንደማይቀበለው በመግለጽ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ማሳወቅ አለበት፡፡
2. ከስምምነቱ መሰረታዊ ዓላማና ግብ ጋር በሚቃረን አኳኂን የተመዘገበ ተአቅቦ ተቀባይነት አይኖረውም፤ በስምምነቱ መሰረት የሚቋቋም አካል የሥራ እንቅስቃሴም አያደናቅፍም፡፡ ከፈራሚ ሀገራት መካከል ሁለት ሦስተኛው የተቃወሙት ተአቅቦ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
3. የተመዘገበው ተአቅቦ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ደብዳቤ በመጻፍ አንስቻለሁ ማለት ይቻላል፡፡ ተአቅቦየን አንስቻለሁ የሚለው ደብዳቤ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ከደረሰ በኂላ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

## አንቀጽ 21

የዚህ ስምምነት ፈራሚ የሆነ ሀገር አባልነቱን ለማቋረጥ ሲወስን በጽሑፍ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ያቀርባል፡፡ አባልነቱም የሚቀረው ጽሑፉ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከአንድ ዓመት በኂላ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 22

በስምምነቱ አተረጓጎም ወይም አፈጻጸም ዙርያ በሁለት ወይም ከሁለት በላይ በሆኑ የስምምነቱ ፈራሚ ሀገራት የሚነሳ ውዝግብ በውይይት ወይም በስምምነቱ በሰፈሩ ሥነ ሥርዓቶች መፍታት ካልተቻለ የጉዳይ ባለቤት ከሆኑት ሀገራት መካከል በአንዱ በኩል ወደ ዓለም አቀፍ የፍትሕ ፍርድ ቤት ለውሳኔ መቅረብ ይችላል፡፡ ይህ መሆን የሚችለው ውዝግብ ውስጥ የገቡት ሀገራት በሌላ የአፈታት ሥርዓት ለጉዳዩ ዕልባት መስጠት ካልቻሉ ነው፡፡

## አንቀጽ 23

1. ስምምነቱን የተቀበለ ማንኛውም ሀገር በማንኛውም ጊዜ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በሚጽፈው ደብዳቤ በኩል በስምምነቱ የማሻሻያ ሃሳብ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አጠቃላይ ጉባኤ የማሻሻያ ሃሳብ ጥያቄ የሚያስተናግድበት ሥርዓት ካለው በዚያ በኩል ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ 24

የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ በአንቀጽ 17 ንኡስ አንቀጽ 1 ለተመለከቱት ሁሉም ሀገራት ስምምነቱን በሚመለከት የሚከተሉትን ጉዳዮች እንዲያውቁ ያደርጋል፤

ሀ/ በአንቀጾቹ መሰረት የሚካሄዱ ፊርማዎች፣ የማጽደቂያና መቀበያ ሰነዶች፤

ለ/ በአንቀጽ 19 መሰረት ስምምነቱ የሚጸናበት ቀን፤

ሐ/ በአንቀጽ 14፣ 20 እና 23 መሰረት የደረሱት መልእክቶችና መግለጫዎች፤

መ/ በአንቀጽ 21 መሰረት የሚቀርብ አባልነት የማቋረጥ ውሳኔ፤

## አንቀጽ 25

1. በቻይንኛ፣ በእንግሊዝኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ሩስያኛና እስፓኒኛ የተዘጋጁ የስምምነቱ ሰነዶች ቅጂዎች እኩል ተቀባይነት ያላቸው ሲሆን፤ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መዝገብ ቤት ይቀመጣሉ፡፡
2. የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ ትክክል መሆናቸው የተረጋገጡ የስምምነቱ ቅጂዎች በዚሁ የስምምነት አንቀጽ 17 ንኡስ አንቀጽ 1 ለተመለከቱት ክፍሎች ያሰራጫል፡፡